# የትምህርት ዓመት 2023/2024 የምዝገባ ጥራዝ

ከዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ጋር በመሆን፣ ለ2023/2024 የትምርህት ዓመት እንኳን ደህና መጣችሁ! እባክዎን ለመጪው የትምህርት ዓመት 2023/2024፣ ይህን የምዝገባ ጥራዝ (packet) ይሙሉ። ደረጃ-በደረጃ የሆኑት ትዕዛዞቶቹ ከዚህ በታች ተካተዋል። በኦንላይን ላይ፣ ሁሉንም ሰነዶች በhttps://enrolldcps.dc.gov/ ያገኛሉ። ትርጉሞችም፤ በአማርኛ፣ በቻይኒኛ፣ በፈረንሳይኛ፣ በስፓኒሽ እና ቬትናም ቋንቋዎች ይገኛሉ። እያንዳንዱ ተማሪ ምንም ዓይነት የኢሚግሬሽን ሁኔታ ወይም የዜንነት ማንነት ቢኖረው፤ በሕዝብ ትምህርት ቤት ውስጥ ገብቶ የመማር መብቱን፣ DCPS ለመጠበቅ በቁርጠኝነት ይሰራል። በመሆኑም፣ DCPS በኮሎምብያ ዲስትሪክት ውስጥ የመኖር ብቃት ያላቸውን ሁሉንም ነዋሪዎች፣ ስለቤተሰቡ የኢሚግሬሽን ሁኔታ ሳይጠይቅ ትምህርት ቤቶቹ ውስጥ ገብተው እንዲማሩ ይፈቅዳል።

በDCPS ውስጥ ያለን ተልዕኮ፣ የተማሪዎቹ የቀድሞ መነሻቸው ወይም ሁኔታቸው ምንም ሆነ ምን፤ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤቶቻችን ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ ትምህርትን በመስጠት፣ ሁሉንም ተማሪዎች በኮሌጅ፣ በስራ መስክ እና በሕይወት ስኬታማ እንዲሆኑ ማዘጋጀት ነው። ሁሉንም ተማሪዎች ማገልገላችን፣ ክብርን እና ደስታን የሚያጎናጽፍ ነገር ሲሆን፣ ሌላ ግሩም የሆነ የትምህርት ዓመት እንዲገጥመን በጉጉት እንጠብቃለን።

## እርምጃ 1. በዚህ ጥራዝ (packet) ውስጥ ያሉትን ቅጾች ይሙሉ

A. የመመዝገቢያ ቅጽ
B. የነዋሪነት ማረጋገጫ ቅጽ
C. የቴክኖሎጂ የዳሰሳ ጥናት
D. የስምምነት መግለጫ ቅጾች (የሚዲያ *ስምምነት እና መልቀቂያ፣ እና ለውትድርና መልማዮች መረጃን*መልቀቅ)
E. የተማሪ እና የወላጅ/አሳዳጊ መብቶች ማስታወቂያዎች
F. የክትባት (Immunization) መስፈርቶች
G. ሁሉን ዓቀፍ የጤና ቅጽ
H. የአፍ ውስጥ ጤና ቅጽ

## እርምጃ 2. ደጋፊ የሆኑ ሰነዶችዎን (supporting documents) ማሰባሰብ።

ተማሪዎን ለማስመዝገብ ጥቂት ደጋፊ ሰነዶች (supporting documents) ብቻ ይፈለጋሉ:

**ለDCPS አዲስ-የሆኑ** (*never previously attended a ከዚህ ቀደም የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤት ውስጥ - በጭራሽ ተምሮ የማያውቅ*)

A. አንድ የዕድሜ ማረጋገጫ ሰነድ – ምሳሌዎቹ የሚያካትቱት፡ የልደት ሰርተፊኬት፣ የሆስፒታል መዝገቦች፣ የቀድሞ የትምህርት ቤት መዝገቦች፣ ፓስፖርት፣ ወይም የጥምቀት ሰርተፊኬት
B. የነዋሪነት ማረጋገጫ – ተቀባይነት ያላቸውን ሰነዶች እና ማረጋገጫ ዘዴዎችን፣ በነዋሪነት ማረጋገጫ ቅጹ ላይ፣ ሙሉ ዝርዝሩን ይመልከቱ
C. የቤት ውስጥ ቋንቋ የዳሰሳ ጥናት – ይህን የዳሰሳ ጥናት ለማግኘት፣ የምዝገባ ቅጹን ይመልከቱ

**አሁን ወደሚማሩበት የDCPS ትምህርት ቤት የሚመለሱ**

- የነዋሪነት ማረጋገጫ – ተቀባይነት ያላቸውን ሰነዶች እና ማረጋገጫ ዘዴዎችን፣ በነዋሪነት ማረጋገጫ ቅጹ ላይ ሙሉ ዝርዝሩን ይመልከቱ

## እርምጃ 3. ጥራዙን እና ደጋፊ ሰነዶችን (support documents)፣ ወደ ተማሪዎ ትምህርት ቤትየምዝገባ ቡድን ያስገቡ።

## እርምጃ 4. ነፃ እና ቅናሽ ዋጋ ያላቸው ምግቦችን (Free and Reduced-Price Meals - FARM) ማመልከቻን ለመሙላት የቀን-መቁጠሪያዎ ላይ ማስታወሻ ያድርጉ።

ነፃ ምሣን ቤተሰቡ እንዲያገኙ ብቁ-መሆኑን ለመወሰን - የ'FARM' ማመልከቻው - ከጁላይ (July) 1 ቀን 2023 ጀምሮ የሚገኝ ይሆናል። ማመልከቻዎቹ በኦንላይን ላይ በhttps://dcps.dc.gov/farm ላይ ወይም በትምህርት ቤታችሁ የእንግዳ-መቀበያ ቢሮ (front office) መገኘት-ይችላል። ሁሉም ቤተሰቦች ማመልከቻውን እንዲያስገቡ ይበረታታሉ።

በDCPS ውስጥ ምዝገባን ለሚጠይቁ እያንዳንዱ ቤተሰቦች፣ ዓመታዊ የዲስትሪክት ነዋሪነት ማረጋገጫን DCPS እንዲጠይቅ ሕጉ የሚያስገድደው መሆኑን እባክዎን

ያስተውሉ። DCPS ይህን የነዋሪነት ማረጋገጫ በምዝገባ ወቅት ያካሂዳል (የነዋሪነት ማረጋገጫው፣ ተማሪው ምዝገባውን ከጠየቀበት መጀመሪያ ቀን ጀምሮ በ**አስር የቀን መቁጠሪያ (ካላንደር) ቀናት** ውስጥ) መረጋገጥ ይኖርበታል። በዲስትሪክቱ መስፈርቶች መሠረት የዲስትሪክት ነዋሪነትዎን ማረጋገጥ ካልቻሉ፣ ወይም ነዋሪ ያልሆኑ የሚከፍሉትን የትምህርት ቤት ክፍያ ለመክፈል ካልቻሉ፣ ተማሪዎ በDCPS እንዳይማር ሊታገድ ወይም ለመገለል አስጊ ሁኔታ ላይ ሊጥለው ይችላል። ለማንኛውም ጥያቄዎች፣ እባክዎን የDCPS የምዝገባ ቡድንን በenroll@k12.dc.gov ያነጋግሩ።

እርስዎ ወይም ልጅዎ በዲስትሪክ-ዙሪያ በሆነ ትምህርት ቤት ውስጥ ካልተመዘገባችሁ ወይም በሎተሪ፣ በልዩ ትምህርት (special education) ማስፈለግ ምክንያት፣ ወይም ሌላ ልዩ ሁኔታዎች ስለገጠማችሁ በዚያ ምክንያት በምትህርት ቤቱ ቦታ ተሰታችሁ እስካለነበረ ድረስ፤ የዲስትሪክቱ ነዋሪነት በተገለጸበት ቦታ ውስጥ የዞን አገልግሎትን በሚሰጥ የDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ፣ እርስዎ እና ልጅዎ በተገቢው ሁኔታ መመዝገብ አለባችሁ። የመማሪያ የዞን ትምህርት ቤትን ለማግኘት፣ አድራሻዎን መማስገባት በሚከተለው ድህረ-ገጽ ላይ ማግኘት ይችላሉ: https://enrolldcps.dc.gov/node/41።

***አድልዎ አልባ ማስታወቂያ :*** *በስቴት እና በፌደራል ሕጎች መሠረት፣ የኮሎምብያ ዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች በእውን ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ወይም በሚታሰብ፤ በዘር፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በዜግነት፣ በፆታ፣ በዕድሜ፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በአካላዊ ገጽታ፣ በፆታዊ አመለካከት፣ በፆታ መለያ ወይም አገላለጽ፣ በቤተሰብ ሁኔታ፣ በቤተሰብ ኃላፊነቶች፣ በትምህርት ደረጃ፣ በፖለቲካዊ ዝንባሌ፣ በዘር አመጣጥ (genetic) መረጃ፣ በጉዳተኝነት፣ በገቢ ምንጭ፣ በቤተሰብ ትስስር ውስጥ ባለ ወንጀል ሰለባ መሆን፣ ወይም ደግሞ በመኖሪያ ወይም በንግድ ስፍራ፣ አማካኝነት አድልዎ አያደርግም። ሙሉ ጽሁፉን እና ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት፣ http://dcps.dc.gov/non-discrimination* ይጎብኙ።